## <u>ከአቶ አንዋር አሕመድ  የቀረበ ጥያቄ፦</u>

1+1+1 =________ ስንት ነው፡ ለክርስቲያኖች?

## <u>ከኢእመ የተሰጠ መልስ፦</u>

ይድረስ፦ ለአቶ አንዋር አሕመድ!

ኢትዮጵያዊ ሰላምታችንን፡ በእግዚአብሔር ስም እናቀርብልዎታለን።

ከዚህ በላይ ላቀረቡት ጥያቄ፡ እንደሚከተለው፡ ተገቢውን መልስ እናበረክትዎታለን፤ የምናበረክትዎትም፡ ከሥጋዊው ይልቅ፡ በመንፈሳዊው የተፈጥሮ አእምሮዎ ተጠቅመው እንደሚረዱት በማመን ነው።

ሰዎች፡ የጻፏቸውን መጽሓፍ ቅዱስን፥ ወይም፡ ቍርዓንን እየጠቀሱ በመከራከር፡ እውነተኛዋ ሃይማኖት አትገኝም። እርስዎና እኛ፡ ሰዎች በፈጠሯቸው እምነቶች ሳይኾን፡ ከእውነተኛዋ የእግዚአብሔር ሃይማኖት ለመድረስ እና እርሷን ለማወቅ የምንችለው፡ በንጹሕ ሰብኣዊ ፍቅር ኾነን፡ በመግባባትና እግዚአብሔር፡ በተፈጥሮአችን፡ በውስጣችን ባኖረው የእውቀት ኃይል፡ በእርጋታ ስንነጋገር ብቻ ነው።

አዩ! የእስልምና ሃይማኖት መሥራችና መሪ የኾነው መሓመድ፡ በጀመረው የሃይማኖት እንቅስቃሴ ላይ፡ ከጣዖት አምላኪዎች ከኾኑ ከአረማውያን አሕዛብ ዘንድ ብቻ ሳይኾን፡ "በእግዚአብሔር እናምናለን!" ከሚሉት፡ ከኦሪታውያኑ አይሁድ እና ከወንጌላውያኑ ክርስቲያኖች ሳይቀር፡ ፈተናና ችግር፥ መከራና ስደት በደረሰበት ጊዜ፡ ቤተሰቡንና ወገኖቹን፡ "ወደኢትዮጵያ ሰዎች (ወደአበሾች) ኺዱ!" ያላቸው፡ ለምን መሰለዎ? እውነተኛዋ የእግዚአብሔር ሃይማኖት የምትገኘው፡ በኢትዮጵያ ስለነበረ ነው።ወደኢትዮጵያ በመጡ ጊዜም፡ ምን ዓይነቱን መልካም አቀባበልና መስተንግዶ እንዳገኙ፥ ወደአገራቸውም በሰላም እንደተሸኙ፥ በኢትዮጵያ የቀሩትም፡ እስከዛሬ ድረስ፡ በሰላምና በደስታ፥ በምቾትና በብልጽግና መኖራቸውን እንደቀጠሉ፡ እርስዎም፡ ይህን እውነታ፡ በእርግጥ፡ እንደሚያውቁ እንገነዘባለን።

ይህን ስንል፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ ሰፍኖ ያለው፡ የአስተሳሰብና የአገዛዝ፥ የአመራርና የአስተዳደር ሥርዓት፡ ያ፡ የእስልምናው ነቢይ መሓመድ፡ ያውቃት የነበረችው፥ እነዚያ ተከታዮቹም፡ በመልካም ተስተናግደው የተሸኙባት፥ ሳይመለሱ የቀሩትም፡ በደኅና የኖሩባት፡ ያች፡ በውስጧ፡ 'ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና' የሚባሉትን የአገልግሎት ዘርፎቿን  የያዘችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ናት!"  ማለታችን አለመኾኑን፡ እዚህ ላይ በአጽንዖት እንዲረዱልን ያስፈልጋል።

በአኹኑ ጊዜ፡ ይህች፡ እውነተኛዋ የእግዚአብሔር ሃይማኖት የምትገኘው፡ የት እንደኾነ፡ እኛ፡ የዚች ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋዮች፡ አረጋግጠን ልናመለክትዎና ልንነግርዎ እንችላለን። አረጋግጠን የምናመለክትዎና የምንነግርዎም፡ <u>የምትገኝበትን</u> ብቻ ሳይኾን፡ <u>የማትገኝበትን</u> ጭምር መኾኑን ልናሳውቅዎ እንወድዳለን።

የማትገኝበትን እናስቀድምልዎ! እውነተኛዋ የእግዚአብሔር ሃይማኖት የምትገኘው፡ የሃይማኖት ድርጅቶች ኾነው፡ በይፋና በሰዎች ሕግጋት በተቋቋሙት፥ እየራሳቸውንም፡ "ኦርቶዶክስ"፥ "ካቶሊክ" እና "ፕሮቴስታንት" እያሉ በሚጠሩት ቤተ ክርስቲያኖች ዘንድ አይደለም። ወይም፡ በውስጡ፡ ጽኑ የእምነት መቃረንን ዐቅፎ፡ በተለያየ ስም በሚጠራው፡ በእስልምና መስጊዶች ዘንድም አይደለም። ወይም፡ እውነትን ሰቅለው ለመግደል በሞከሩ፡ በኦሪታውያኑ አይሁድ ምኵራቦችም ዘንድ አይደለም። ወይም፡ ልዩ ልዩ የመናፍስትንና የፍልስፍናን፣ የአረማዊነትንና የጣዖትን አምልኮ፡ በይፋ በሚያካኺዱት፡ በአሕዛብ ቤተ እምነቶችም ዘንድ አይደለም። ሰዎች በጻፏቸው፡ በመጽሓፍ ቅዱስ፥ ወይም፡ በቍርዓን፥ ወይም፡ እነርሱን በመሰሉት መጻሕፍትም ውስጥ፡ እውነተኛዋ የእግዚአብሔር ሃይማኖት አትገኝም።

አኹን ደግሞ፡ የምትገኝበትን፡ እናስከትልልዎ! እውነተኛዋ የእግዚአብሔር ሃይማኖት፡ ጥንትም፥ ዛሬም፥ ለዘለዓለምም የምትገኘው፡ በእርስዎ እና በእኔ ሰውነት ውስጥ ነው፤ ይህን እውነታ፡ በእየራሳችን የምናረጋግጠው፡ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር፡ ከእርሱ ከፍሎ ያወጣቸውን፡ ነፍስን፥ ሥጋንና መንፈስን፡ ለእያንዳንዳችን ሰጥቶ፡ በመልኩ በፈጠረን ጊዜ፡ በየልቦናችን ላይ በጻፋቸው ቃሎቹ አማካይነት፡ ያች፡ እውነተኛዋ የእግዚአብሔር ሃይማኖት፡ ሕያው ኾና፡ በውስጣችን የምትገኝ፥ ለሌሎችም፡ ራሷን ገልጻ ለማሳወቅና ለመናገር የሚቻላት ኾነች።

ስለዚህ፡ በእኛ በኩል፡ ከእርስዎ ጋር መወያየት የምንፈልገው፡ በዚህ ኹኔታ ስለኾነ፥ የእርስዎም ፈቃድ፡ ይህ እንዲኾን፡ በአክብሮት እንጠይቅዎታለን። እንግዴህ፡ በዚህ ረገድ ያለው፡ የእርስዎ ፈቃድ፡ "እንደእኛው ኾኗል!" ብለን በማመን፡ 1+1+1=__________ ማለትም፡ "ለክርስቲያኖች፡ ፩ እና ፩ እና ፩ ሲደመሩ፡ ስንት ይኾናሉ?" ብለው ላቀረቡት፡ ሒሳባዊ ጥያቄ፡ ሃይማኖታዊው መልሳችን፡ 1+1+1= "1 ነው!" በሚል ቍርጥ ቃል፡ እውነተኛውንና ትክክለኛውን መልስ፡ በአጽንዖት የምንሰጥዎ፡ በእርስዎ ዘንድ ተሰሚነትን እንደምናገኝ በመተማመን ነው።

ምናልባት፡ በእርስዎ በኩል፡ ከእኛ የጠበቁት ውጤት፡ በሥጋዊው የአእምሮ አስተሳሰብ፡ 1+1+1=3 የሚለውን ከኾነ፡ "በጣም ተሳስተዋል!" ማለት ነው። ምክንያቱም፡ ረቂቅ የኾነውን፡ የሃይማኖትን ነገር፡ ግዙፍ አስመስሎ በመቍጠር፡ በሥጋዊ አእምሮ፡ ማስረዳትም፥ መረዳትም፡ የማይቻል በመኾኑ ነው። ይህን ሃይማኖታዊ እውነታ፡ ለማስረዳትና ለመረዳት የሚቻለው፡ በመንፈሳዊው አእምሮ ብቻ ነው። እርስዎ፡ በዚህ፡ የእግዚአብሔር ነገር ላይ፡ መወያየታችንን እንድንቀጥል ከፈለጉ፡ እርስዎም፡ እንደእኛ፡ በመንፈሳዊው አእምሮዎ ብቻ ለመጠቀም፡ የተዘጋጁ መኾን አለብዎት።

ይህን ምሥጢር፡ በጥቂቱም ቢኾን፡ እንድንገልጽልዎ ከፈቀዱ፡ እርስዎ ራስዎ ባመጡት፡ የጥያቄ ዓይነት በመጠቀም፡ እውነታውን እናቅርብልዎ! ይኸውም፡ እንዲህ ነው፡- እንደሚያይዋት፡ "፩"፥ ወይም፡ "1"፡ በአካሏም፥ በባሕርይዋም፡ ያው አንድ ኾና፡ በአንድነት የምትታይና የምትጠራ፡ አንዲት ነገር ናት።

እርሷን፡ እንኳንስ፡ አንድ አንድ ጊዜ ቀርቶ፡ ኹለት ጊዜያት፡ "፩"፡ "፩"፥ ወይም፡ "1"፡"1"፤ ደግሞም፡ ሦስት ጊዜያት፡ "፩"፡ "፩"፡ "፩"፥ ወይም፡ "1"፡ "1"፡ "1"፤ ከዚህም በላይ፡ መቶ፥ ወይም፡ ሺ ጊዜያት፡ መላልሰው ቢጽፏት፡ ያችው፡ አንድ፡ "፩"፡ "1" ናት እንጂ፡ ኹለት፡ ፪፡ 2፥ ወይም፡ ሦስት፡ ፫፡ 3 አትኾንም፤ ልትኾንም አትችልም።

እስኪ፡ አኹን ደግሞ፡ ራስዎን፡ በምሳሌነት እንድንወስደው ይፍቀዱልንና ይመልከቱት! ይህን ራስዎን፡ የትም ቦታ፥ ኹለት፥ ሦስት፥ ዐሥር፥ ሃያም ቦታ ቢኾን፡ ወስደው ቢያስቀምጡት፡ ያው፡ አንድ፡ እርስዎ ነዎት እንጂ፡ ኹለት፥ ሦስት፥ ከዚያም በላይ ሊኾኑ፡ ከቶ አይችሉም።

አኹን እንኳ፡ ከእኔ ጋር፡ እንዲህ ስንጻጻፍ፡ እርስዎ፡ በአካል ያሉት፡ እቤትዎ ነው። ነገር ግን፡ እኔ ዘንድ እኮ መጥተው፡ አጠገቤ አሉ፤ አይዎታለሁ። እንዴት ቢሉኝ? "1+1+1 =________ sente new le christeyanoche" ብለው በጻፏቸው አኀዛት (ቊጥሮች) እና በሌሎቹ ቃላቶችዎ አማካይነት፡ እኔ ዘንድ መጥተው፡ አግኝቼዎታለሁ። ይህ ብቻም አይደለም፤ አኹን፡ እኔ፡ ይህን መልስ በምጽፍልዎ ጊዜ፥ ወይም፡ ስለእርስዎ በማስብበት ጊዜ ኹሉ፡ እርስዎን፡ በመንፈስ አይዎታለሁ። እዚያ፡ እቤትዎ፡ በአካለ ሥጋ እንዳሉ ኹሉ፡ እዚህ፡ እኔም ዘንድ፡ በመንፈሳዊው አካልዎ አሉ። እርስዎ፡ ከእግዚአብሔር የተሰጠዎትን፡ ይህን የመሰለውን ጸጋ ባያውቁት ነው እንጂ፡ እኔም፡ በእርስዎ ዘንድ፡ እንዲሁ የምገኝ ነኝ።

ይህ ማለት፡ እርስዎ፡ በአካልዎ፥ በጽሑፍዎ እና በመንፈስዎ አማካይነት፡ እኔ ዘንድ ስላሉ፡ "፫ (3) ነዎት!"፥ ወይም፡ "ኾነዋል!" ማለት አይደለም። ያው፡ የነፍስ፥ የሥጋና የመንፈስ የኾኑ፡ ሦስት መገለጫዎች ባሕርያት ያሉት፡ አንድ ሰው ነዎት እንጂ፡ ሦስት አይደሉም። አንድ ነዎት።

እንደዚሁ ኹሉ፡ <u>እግዚአብሔር፡ ፩ (1) አንድ ነው እንጂ፡ ፫ (3) ሦስት አይደለም።</u> ነገር ግን፡ በምሳሌነት በቀረበው፡ በእርስዎ እውነተኛ የምንነትና የማንነት ኹኔታ እንደታየው ኹሉ፡ ያ አንዱ እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያ፡ <u>"እግዚአብሔር አብ"</u>፥ ወይም፡ "አባት" ተብሎ፡ በመንበሩ ላይ ተቀምጦ አለ።

እንዲህ፡ በመንበሩ ተቀምጦ ያለ ሲኾን፡ በመንፈሱ አማካይነት፡ በእርስዎና በእኔ፥ በፍጥረቱም ዘንድ ሞልቶ ይገኛል። የሚገኘውም፡ ራሱ ነው እንጂ፡ ከራሱ ከፍሎ የሚልከው፡ ከእርሱ ያነሰ፡ ሌላ መልእክተኛ አይደለም። በዚያ፡ "ምሉዕ በኵለሄ"፥ ማለትም፡ "በኹሉ የመላ" በኾነበት ምንነቱና ማንነቱ፡ <u>"እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ"</u> ይባላል። ያም፡ ያው፡ እርሱ ራሱ፡ እግዚአብሔር አብ ነው እንጂ፡ ሌላ አይደለም።

ያ አንዱ እግዚአብሔር፡ በፈጠረው ፍጥረቱ ላይ ባለው፡ የፈጣሪነት ባለቤትነትና የመሪነት ኃላፊነት፥ የመጋቢነት ሥልጣንና የጥበቃ ተግባር ረገድ ያለበትን ግዳጅ፡ በሥርዓት ለማካኼድ ሲል፡ ራሱን ምን እንዳደረገ፡ ቸርነቱን ይመልከቱ!

ደግሞም፡ ጥንቱኑ መልካም አድርጎ፥ በፍትሕ ርትዕትም አከናውኖ የፈጠረውን ፍጥረት፡ ለማቃወስና ለማበላሸት፡ ከምድራዊው ፍጥረተ ዓለም በፊት፡ የክፋት መንፈስ ኾኖ በተቃዋሚነት የተነሣበትን፡ ፍጡሩን ሰይጣንን ለመቋቋም ሲል፡ ራሱን ምን እንዳደረገ፡ ትሕትናውን ይመልከቱ!

በመጨረሻም፡ እውነተኛዋን የእግዚአብሔር ሃይማኖትና ምግባሯን፡ ለሰብአዊው ፍጡሩ ከማስተማር ጋር፡ ማንም ፍጡር ሊከፍለው የማይችለውን መሥዋዕትነት፡ በራሱ ቤዛነት በመክፈል፡ ያ፡ "ዲያብሎስ" የተባለው፡ የክፋት መንፈስ፡ በፍጥረቱ ላይ ያደረሰውን ጥፋት አስወግዶ፡ በተለይ፡ በድክመቱ የጠፋውን የሰውን ዘር፡ ከክፋት፥ ከኃጢኣትና ከዘለዓለም ሞት ለማዳን ሲል፡ ራሱን፡ ለእንዴት ዓይነቱ ሥቃይ አሳልፎ እንደሰጠ፡ ፍቅሩን ይመልከቱ!

ይኸውም፡ ከፍጥረተ ዓለም በፊት፡ "እግዚአብሔር ወልድ፥ እግዚአብሔር ቃል"፡ ማለትም፡ "የእግዚአብሔር ልጅ፥ የእግዚአብሔር ቃል" መኾንን፥ በፍጻሜ ዘመንም፡ "ኢየሱስ መሢሕ" ተብሎ፡ ራሷን፡ ለአምላክ እናትነት ካበቃችው፡ ከአንዲት ኢትዮጵያዊት ድንግል ማርያም በሰውነት መወለዱ ነው።

**እንዲህ፡ አንድ የኾነው እግዚአብሔር፡ ፍጥረቱን የፈጠረው፥ የጠበቀውና ያዳነው፡ እንዲህ አድርጎ፡ በሦስትነት ያገልግሎት መገለጫው መኾኑን፡ ፍጡሮቹ አውቀው፡ ሊያመሰግኑት ይገባቸዋል።**

ለአኹኑ፡ ይህ ይበቃ ይመስለናል።